# የታህሳስ ሶስት መታሰቢያ ዴሞራሲያዊ ንቅናቄ
# December 3 Commemoration Democratic Movement

## የሕዝብን ሕዝባዊ ዐመፅ ዐዋጅ አያቆመውም!

ባለፈው መስከረም 22 ቀን 2009 ዓ.ም. በሰላም ፈጣሪያቸውን ለማመስገን በተሰበሰቡ ንጹሃን ወንድሞቻችን ላይ የተፈጸመውን የጅምላ ጭፍጨፋ ከፉኛ እናወግዛለን፡፡

በገዛ ሃገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ የመጨፍጨፍን ገፈት የቀመስነው እኛ የጋምቤላ ልጆች ዛሬ በኦሮሞ ወገኖቻችን ፣ በኦሮምያ እና በጎጃም ፣ በጎንደር አማራ ዜጎቻችን ላይ እየተደረገ ያለው የዘር ማጥፋት ወንጀል ከፉኛ አሞናል። ለዚህም ነው ደማችሁ ደማችን ነው ስቃያችሁ ስቃያችን ነው እያልን ከልብ የመነጨ ሀዘናችንን የምንገልጸው፡፡

ዛሬ ሀዘን ቢያቆራምደንም በአንድ በኩል ደግሞ ከጠላታችን ከወያኔ ጋር እየተናነቅን መስዋዕት የሚከፍል ትውልድ መፈጠሩን ስንመለከት እንባችንን አድርቆ ኢትዮጵያዊ ወኔያችንን ከፍ ያደርግልናል፡፡

ለሀያ አምስት ዓመታት ፣ በጋምቤላ አኝዋክን ከመፍጀት ጀምሮ ፣ ቤንሻጉልን ጠርጎ ፣ ኢሉባቡር ቴፒዎችን መሬት ለመንጠቅ ፈጅቶ ፣ አፋርን ትግራይ ለማድረግ እንደለመደው መንጥሮ መንጥሮ ዛሬ ደግሞ ማንነቴን ያለውን የጎንደርን ወልቃይቶችን በግድ ትግሬ ካልሆንክ በሚል አይን ያውጣ አሳፋሪ ተግባር ላይ ተሰማርቶ ያለው ወያኔ ፣ የሕዝብ አመጽ በዐራቱም ማእዘን ተቀጣጠለበት፡፡ ከዚህ ቀደም ፣ ያለ ዐዋጅ እንዳልጨፈጨፈ ዛሬ አስቸኳይ ዐዋጅ አወጅኩ ቢል የጦር አዋጅህ ከሞት አያድንህም የሚል መልእክታችንን እናስተላልፍለታለን፡፡ እኛ በታህሳስ ሶስት ሁለት ሺ ስድስት ዓመተ ምህረት በጋምቤላ በጅምላ የተጨፈጨፉ አኝዋኮችን መታሰቢያ አድርገን የምንቀሳቀስ የጋምቤላ ተወላጆች ለኢትዮጵያውያን ድርጅቶችና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባጠቃላይ የምናስተላልፈው መልእክት በዓለም ላይ ማንም አጋራችን ነው ብለን የምንጠራው የባእድ መንግስት የሌለን በመሆኑ በሞት አፋፍ ላይ ያለውን የወያኔ አገዛዝ ቀብረን ለመገላገል ያለው አማራጭ እጅ ለጅ ተያይዘን እንደ አንድ ኃይል በጋራ መታገል ብቻ ነው። ዓላማችን ኢትዮጵያችንን አድነን፤ ሕዝባችንን ከጥፋት ታድገን በእኩልነት ላይ የተመሰረተች ኢትዮጵያን መመስረት ሊሆን ይገባዋል።

የተለያዩ ሃይማኖታችንን የብሔርም ሆነ የቋንቋ ልዩነታችንን፤ ጉራማይሌ ቀለማችንን እንደ ውበት ቆጥረን ኢትዮጵያን ለማዳን በሚደረገው የሕብረት ትግል እኛም እንደ ዜጋ በአንድነት የሚከፈለውን መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆናችንን በሚሰዋው ሕዝባችንና በታሪካዊቷ ኢትዮጵያ ስም ቃል እንገባለን፡፡ በየስርአቱ የተለያዩ በደሎች ቢኖሩም የበደሉን የየጊዜው የነበሩት የአገዛዝ ስርአቶች እንጂ ኢትዮጵያችን አይደለችም እና የጋራ ሀገራችንን በጋራ እናድን እያልን ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!